**Kinijit North America Association of Support Organizations (KNAASO)**
**የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ማህበር**

# የመልካም ምኞት መግለጫ

ታህሳስ 22 ቀን፣ 2000 ዓ.ም
ጃንዋሪ 1 ቀን 2008 ዓ. ም

*ውድ የቅንጅት ደጋፊዎች*

*ያለፈው አመት በኢትዮጵያ ውስጥ የህግ ስርአቱ ለፈተና የቀረበበት፣ የዲሞክራሲ ሃይሎች ለህግ የበላይነትና ለፍትህ መከበር ያላቸውን የማያወላውል አቋምና የትግል ስሜት የገለጹበት፣ አመት ነበር:: በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ለሃገራችን ያለንን ፍቅርና ስሜት፣ ለቅንጅት ያለንን ድጋፍ፣ በግፍ ለታሰሩ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች መፈታት፣ ታሪክ ሲያስታውሰው የሚኖር ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገናል::*

*በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ ኢትዮጵውያን በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የሰብአዊ መብት መከበርና የህግ የበላይነት መረጋገጥ ሊረዳ የሚችል፣ ዲፕሎማሲያዊ ጫና ለመፍጠር የሚያስችል፣ ኤች አር 2003 የተሰኘ የህግ ረቂቅ የአሜሪካ ምክር ቤት ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ መቻል በህብረታችን የጋራ ጥንካሬያችንን አስመስክረናል::*

*በጸሃይ፣ በብርድ፣ በቀንና በጨለማ እየተንከራተትን፣ አቤቱታና ድምጻችንን ያሰማንበት፣ በመላው አለም ከአገራቸው ውጭ ለሚኖሩ ዜጎች ምሳሌ የሚሆን ጠንካራ የትግል አጋርነት አሳይተናል:: በዚህም የቅንጅት መሪዎች ተፈተው በመካከላችን ተገኝተው የጥረታችንን ፍሬ በከፊል ተመልክተናል::*

*በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ለረጅም ጊዜ በሃገራችን ውስጥ ለውጥ አንዲመጣ በተለያዩ ቡድኖች በመሰለፍ ድጋፋችንን ስንሰጥ ቆይተናል:: ባለፉት ሶስት አመታት ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ ሆኖ ተስፋ ያሳደረውን ቅንጅትን፣ ማንነቱን አውቀን፣ የሃሳብ ጥራቱን ተቀብለን፣ በግለሰብ ትውውቅ፣ በቡድን ትስስር ሳይሆን በአላማ አንድነት ተሰባስበን ተንቀሳቅሰናል::*

*ይህም ሆኖ ግን፣ ባጠቀላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰፍን ይገባዋል ብለን የምንመኘውን ዴሞክራሲያዊ አሰራር ተግባራዊ በሚያደርጉና፣ ኋላ ቀር አመለካከትን፣ አምባገነንነትን፣ ጠባብ የቡድን ስሜትን፣ ሴራንና አድርባይነትን እንዲያንሰራራ በተሰለፉ ቡድኖች መካከል የከረረ ውጥረት ተፈጥሮአል:: ይህ ጉዳዩን በጥልቀት ባላወቁ ወገኖች ላይ መጠነኛ መደናገር መፍጠሩ የሚካድ አይደለም:: ደግነቱ በጥላቻ ፖለቲካና ደባ ዙሪያ የተጠነጠነው እንቅስቃሴ አራማጆች እየተጋለጡ በመምጣታቸው በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵዊ ትክክለኛውን አማራጭ በመውሰድ ለዲሞክራሲያዊሃይሉ ድጋፉን በማጠናከር ላይ ይገኛል::*

*በዚህ አመት ለተደረጉት በጎ ተግባራት ሁሉ አስተዋጽኦ ያደረጋችሁ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ የዜና ማሰራጫዎች፣ በቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማህበርና በራሴ ስም ልባዊ ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ:: ቀጣዩ ፈተና በርካታ ድርጅታዊና ሃገራዊ ጉዳዮች የሚወሰኑበት ስለሚሆን ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን የኢትዮጵያን ህዝብ ተስፋ ሊያለመልሙ የሚችሉ ስራዎች ላይ በህብረት ዴሞክራሲያዊ ከሆኑ የቅንጅት መሪዎች ጋር በጋራ እንድንሰራ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ::*

*በተለያዩ ምክንያቶች ከቅንጅት ተግባራዊ እንቅስቃሴ እራሳችሁን ያገለላችሁ፣ የኢትጵያን ህዝብ ትግል እንዳይሸረሸር በሚረዳ መልኩ በጋራ እንድንሰራ ልባዊ ጥሪዬን አቀርባለሁ::*

*በህብረታችንና በትግላችን በኢትዮጵያ ውስጥ አስተማማኝ የዴሞክራሲ ስርአት እንዲመሰረት እናደርጋለን!*

*መጭው አመት የሰላም የፍቅርና የጤና እንዲሆን ምኞቴ ነው::*

*አክሎግ ልመንህ*
*የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ማህበር ሊቀመንበር*